የሰ/መ/ቁ 71375

ጥር 16 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- ዳሽን የህትመትና የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ነ/ፈጅ አቶ ትዕዛዙ

ዓለማሁ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ፍስሐ ይሁን - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የአሁኑ የሰበር አመልካች በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሳሽ ሲሆን ተጠሪው ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም ከተከሳሽ ጋር ባደረግነው ውል ከሳሽ ለተከሳሽ ፍስሐና ስራው የሚል መፅሐፍ 300 ቅጂ ለማዘጋጀትና ተከሳሽም ለከሳሽ ብር 50,000 (ሀምሳ ሺህ ብር) ለመክፈል የተስማማን ሲሆን በስምምነታችን መሰረት ተከሳሽ ቅድመ ክፍያ ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) ከፍሎ መጽሐፎቹን ከሳሽ አዘጋጅቼ ባጠናቅቅም ቀሪውን ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) ሳይከፍለኝ ከአንድ ዓመት በላይ ስለቆየ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍለኝ ይወሰንበት የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም ሞቷል በመባሉ ወራሾች ካሉ ቀርበው ለክሱ መልስ እንዲሰጡ መጥሪያ በተከሳሽ ቤት ተለጥፎ ወራሾች ባለመቅረባቸው ክርክሩ በሌሉበት ቀጥሎ የመ/ደ/ፍ/ቤቱ መዝገቡን በመመርመር በሰጠው ፍርድ ከሳሽ ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ሁሉም በከሳሽ የተጻፉ ናቸው፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች ደግሞ እንደ ማስረጃ ሆነው የሚቀርቡት በራሱ በከሳሽ እንጂ በተከሳሽ ላይ አይደለም፡፡ ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ግዴታ ስለመኖሩ በማንኛውም ማስረጃ በበቂ ሁኔታ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ በመካከላቸው አስገዳጅ ውል መኖሩን ባላስረዳበት እንደውሉ እንዲፈጸምለት ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ መልስ ሰጪን መጥራት ሳያስፈልግ የይግባኝ ባይን የይግባኝ መዝገብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት ይግባኝ ባዩን አሰናብቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አመልካችም በመ/ደ/ፍ/ቤት ፍርድም ሆነ በከ/ፍ/ቤት ትዕዛዝ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሰው

ቅሬታ የህትመት ስራ ውል በቃል ጭምር ማድረግ የሚቻል ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤቶች በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሊያስገድዳቸው የሚችል የጽሁፍ ውል የለም ሲሉ ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡

በሰበር ደረጃም የተጠሪው ወራሾች ቀርበው መልስ እንዲሰጡ የፍ/ቤቱ መጥሪያ የደረሳቸው ቢሆንም ቀርበው  መልስ ባለመስጠታቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

አመልካች ያቀረበው ክርክርና በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ፍርድ ከዚህ በላይ የተገለጸ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካችና በስር ተከሳሽ መካከል አስገዳጅ ውል ስለመኖሩ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ የለም ሲሉ ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ለስር የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሉ ስለመኖሩ በማስረጃነት ያቀረባቸው የጽሁፍ ሰነዶች ቅድመ ክፍያና ተጨማሪ ክፍያ ከተከሳሽ የተቀበላቸውን ደረሰኞችና አመልካች ለተከሳሽ የጻፈውን የዋጋ ማቅረቢያ ነው፡፡ ከእነዚህ ሰነዶች በስተቀር ውሉ በጽሁፍ የተደረገ ስለመሆኑ ያቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ የለም፡፡ በፅሁፍ የተደረገውን ውል አለማቅረብ ደግሞ በውል ሰጪና ውል ተቀባይ መካከል ውል የለም ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም በፍ/ህ/ቁ/1681(1) እንደተደነገገው ውል በቃል ወይም በጽሁፍ ወይም በተለመዱ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ለውሉ መነሻ ከሆነው ምክንያት የተነሳ ግዴታ መግባት መፍቀድን በማያጠራጥር አሰራር በማስታወቅ ጭምር መግባት ስለሚቻል ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን ሁሉም የውል ዓይነቶች በቃል ወይም በተለመዱ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ግዴታ ለመግባት መፍቀድን በማያጠራጥር አሰራር በማስታወቅ ይደረጋሉ ማለት አይደለም፡፡ ለዚህም የ/ፍ/ህ/ቁ/1725ን መመልከት ተገቢነት አለው፡፡ በዚህ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት ለብዙ ጊዜ የሚቆዩ ውሎች፤ እንዲሁም የዋስትና ውሎች፤ የኢንሹራንስ ውሎች እና ህጉ በግልጽ በጽሁፍ እንዲደረጉ የሚያስገድዳቸው የውል ዓይነቶች ሁሉ በጽሁፍ መደረግ አለባቸው፡፡

ይህንኑ የህግ አነጋገር ይዘን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ከስር ተከሳሽ ጋር ገብተናል በሚለው የህትመት ስራ ውል ውሉ በፅሁፍ እንዲሆን የሚያስገድድ የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ አመልካች ከስር ተከሳሽ ጋር ገብተናል የሚለው ውልም በገቡት ውል መሰረት 300 ቅጂ መጽሀፎችን አባዝቶ ከመስጠት ያለፈና ለረጅም ጊዜ ይቆያል ተብሎ የማይገመት በመሆኑ የውሉ በጽሁፍ መሆን የግድ የሚያስፈልግ አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የስር ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረባቸውን አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመመርመር እንዲሁም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/264(2) እንደተደነገገው ውሉ ከዚህ በላይ በተጠቀሱ መንገዶች የተደረገ መሆን ስላለመሆኑ፣ በውል ሰጪና ውል ተቀባይ መካከል አለ ስለተባለው የውል ግንኙነት አመልካች ባቆይቆጠራቸውም እንኳን ምስክሮችን መስማት ጠቃሚ መስሎ ከታየ አስቀርቦ መስማት በጉዳዩ ላይ ፍርድ ለመስጠት የሚያስችሉ ፍሬ ነገሮችን በአግባቡ አጣርተው ተገቢውን ፍርድ መስጠት ሲገባቸው ይሄንኑ በማለፍ አመልካች አስገዳጅ ውል መኖሩን አላስረዳም  በሚል ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ባለመሆኑ የሰጡት ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 69348 በቀን 26/08/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 110517 በቀን 23/10/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. አመልካች ከስር ተከሳሽ ጋር አድርገናል በሚለው የህትመት ውል መሰረት ፍስሐና ስራው የሚል 300 ቅጂ መጽሐፎችን ማዘጋጀቱንና አለማዘጋጀቱን የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 272 መሰረት ምትክ ዳኛ እስከ ቦታው ድረስ በመላክ ምትክ ዳኛው ተገቢውን ምርመራ አድርገው በሚያቀርቡት የምርመራ ውጤት መሰረት የበኩሉን ፍርድ በጉዳዩ ላይ እንዲሰጥ ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/343 (1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሱን ይቻል ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት.ዘ